# ድመት ፣ ውሻ እና እንቁላል



Amharic

ድመት፣ ውሻ እና እንቁላል

ጽንሰ-ሐሳብ፣ ጽሑፍ፣ ስእሎች እና ዲዛይን፤

በኤልኬ እና ሬኔ ሌስኪን

አርትኦት

ኤስ አይ ኤል - ትምህርት ለሕይወት

ይህን መጽሐፍ በኤሌክትሮኒክስ በትረካ ለማግኘት

www.mytalkingbooks.org ይጎብኙ

# ድመት ፣ ውሻ እና እንቁላል

Amharic
Ethiopia

Copyright © 2025, SIL Ethiopia

http://creativecommons.org/licenses/by-nc-sa/4.0/
You may not use this work for commercial purposes. You may adapt and add to this work, but you may distribute the resulting work only under the same or similar license to this one. You must keep the copyright and credits for authors, illustrators, etc.

Concept, text, illustrations and design;
Elke and René Leisink
Translator: Biruktawit Girma



ይሔ ድመት ነው። ይሔ ዉሻ ነዉ።



ድመት እና ውሻ እየተራመዱ፤

በመንደራቸው ውስጥ ይሄዳሉ።



ከዚያም እንቁላል ያያሉ። እንቁላሉ በሳር ውስጥ ነው። እንቁላሉ በሳር ውስጥ ብቻውን ነው።



ድመት እና ውሻ ወደ ወፍ ሄደዉ፤ ወፏን
"ይህ የአንቺ እንቁላል ነው?" ብለው
ጠየቋት። ወፏ ግን ፤ "አይ፤ የእኔ እንቁላል
አይደለም።" አለች።



ድመት እና ውሻ ወደ ጉጉት ሄደው፤
ጉጉቷን "ይህ የአንቺ እንቁላል ነው?"
ብለው ጠየቋት።



ጉጉቷ ግን "አይ፤ ይህ የእኔ እንቁላል
አይደለም" አለች።



"ዝይውን ጠይቅ። ምናልባት እንቁላሏ ሊሆን ይችላል።"



ድመት እና ውሻ ወደ ዝይ ሄደው። ዝይውን
"ይህ የአንቺ እንቁላል ነው?" ብለዉ
ጠየቋት።



ዝይው ግን "አይ፤ የኔ እንቁላል አይደለም
ሁለቱን ዳክዬዎች ጠይቋቸው ምናልባት
የነሱ እንቁላል ሊሆን ይችላል" ብላ
መለሰች።



ድመት እና ውሻ ወደ ሁለቱ ዳክዬዎች ሄደው፤ ሁለቱን ዳክዬዎች "ይህ የእናንተ እንቁላል ነው?" ብለው ጠየቁ። ሁለቱ ዳክዬዎች ግን "አይ፤ ይህ የእኛ እንቁላል አይደለም።" ብለው መለሱ።



ከዚያም እንቁላሉ ተሰበረ።



በእንቁላል ውስጥ እንሽላሊት ነው ያለው።

ሕፃን እንሽላሊት።

ሕፃኗ እንሽላሊት "እናቴ የት ናት? አባቴ
የት ነው? እናቴ እና አባቴ የት አሉ?
አለች።



ድመት እና ውሻ ሕፃኗን እንሽላሊት ወደ

እናት እና አባቷ ወሰዷት።



ቻው–ቻው ድመት.

ቻው–ቻው ውሻ።

ቻው–ቻው ሕፃን እንሸላሊት።

Let's grow a library
Bloom®